# ምዕራፍ አንድ

## የከተማችን መገኛ

- **አቅጣጫ (Direction):**
    - አቅጣጫ ማለት አንድ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ግለሰብ ወይም ነገር የሚጓዝበት የፍሰት መስመር ወይም ፊቱን ያዞረበት መስመር ማለት ነው።
    - መሰረታዊ አቅጣጫዎች ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ናቸው። በተጨማሪም በስተግራ፣ በስተቀኝ፣ ከበስተኋላ፣ ከበስተፊት፣ ከላይና ከታች በማለት መግለጽ ይቻላል።
    - በካርታ ላይ አቅጣጫን የሚያሳይ ምልክት አብዛኛውን ጊዜ የሰሜን አቅጣጫን የሚያመለክት ቀስት ነው።
- **ካርታ (Map):**
    - ካርታ የመሬትን ገጽታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚያሳይ በዝርግ ወረቀት ላይ የሚሳል ስዕላዊ መግለጫ ነው።
    - የቦታዎችን መገኛ፣ ርቀት፣ ስፋትና አቅጣጫ ለማወቅ ይጠቅማል።
    - **መስፈርት** (Scale): በመሬት ላይ ያለ ርቀት እና በካርታ ላይ ያለ ርቀት ንጽጽር ወይም ጥምርታ ማለት ነው።
- **አንጻራዊ መገኛ (Relative Location):**
    - የአንድን ስፍራ መገኛ በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች ነገሮች (ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ) ጋር በማነጻጸር የሚገለጽበት መንገድ ነው።
    - አዲስ አበባ በመሀል ኢትዮጵያ የምትገኝ ሲሆን፣ በሁሉም አቅጣጫ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ልዩ ዞን የተከበበች ናት።

LIVEWORKSHEETS

- **ፍጹማዊ መገኛ (Absolute Location):**
    - የአንድን ስፍራ ትክክለኛ መገኛ በኬክሮስና በኬንትሮስ የአሀዝ ልኬት (ዲግሪ) አማካኝነት መግለጽ ነው።
    - **ኬክሮስ (Latitude):** ከምድር ወገብ በስተ ሰሜንና ደቡብ የሚለካ ማዕዘናዊ ልኬት ነው።
    - **ኬንትሮስ (Longitude):** ከትልቁ ሜሪዲያን በስተ ምዕራብና ምሥራቅ የሚለካ ማዕዘናዊ ልኬት ነው።
    - የአዲስ አበባ ፍጹማዊ መገኛ በ $9^{\circ} 1^{\prime} 48^{\prime \prime}$ በስተ ሰሜን እና በ $38^{\circ} 44^{\prime} 24^{\prime \prime}$ በስተ ምሥራቅ ላይ ይገኛል።
- **የአዲስ አበባ መልክዓ ምድራዊ ገጽታ:**
    - አማካይ የከፍታ መጠን ከባህር ጠለል በላይ 2400 ሜትር ነው።
    - ከፍተኛው ቦታ የእንጦጦ ተራራ (ከ3200 ሜትር በላይ) ሲሆን፣ ዝቅተኛው ደግሞ የቦሌ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ አካባቢ ነው።
- **ዋና ዋና ቦታዎች:**
    - በከተማዋ የተለያዩ ታሪካዊ ቅርሶች (እንደ አጼ ምኒልክ ሐውልት፣ የሰማዕታት መታሰቢያ)፣ ገበያዎች (መርካቶ)፣ እና መዝናኛዎች (አንድነት ፓርክ፣ ወዳጅነት አደባባይ) ይገኛሉ።
- **የመረጃ ቴክኖሎጂ (Information Technology):**
    - ስለ ስፍራዎች መገኛ፣ ርቀትና አቅጣጫ መረጃ የሚሰጡ ቴክኖሎጂዎችን (እንደ ጂ.ፒ.ኤስ (GPS)፣ ጎግል ካርታ (Google Map) እና ጎግል ኧርዝ) መጠቀም መገኛን ለማወቅ ይረዳል።

LIVEWORKSHEETS

# የሙከራ ጥያቄ ከፍል አንድ

**ክፍል አንድ፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

1. የመሬትን ገጽታ በዝርግ ወረቀት ላይ የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ ምን ይባላል?

   ሀ. ሉል ለ. ካርታ ሐ. ንድፍ መ. ፎቶግራፍ

2. ከአራቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች አንዱ ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ሰሜን ለ. ደቡብ ሐ. ሰሜን ምሥራቅ መ. ምዕራብ

3. በካርታ ላይ አብዛኛውን ጊዜ የቀስት ምልክት የሚያሳየው ወደ የትኛው አቅጣጫ ነው?

   ሀ. ደቡብ ለ. ሰሜን ሐ. ምሥራቅ መ. ምዕራብ

4. የአንድን ቦታ መገኛ በኬክሮስና በኬንትሮስ መግለጽ ምን ይባላል?

   ሀ. አንጻራዊ መገኛ ለ. ተፈጥሯዊ መገኛ

   ሐ. ፍጹማዊ መገኛ መ. ሰው ሰራሽ መገኛ

5. ከምድር ወገብ በስተሰሜንና ደቡብ የሚለካ ማዕዘናዊ ልኬት ምን ይባላል?

   ሀ. ኬንትሮስ ለ. ሜሪዲያን

   ሐ. ኬክሮስ መ. መስፈርት

6. አዲስ አበባ በሁሉም አቅጣጫ በየትኛው ክልል ተከባ ትገኛለች?

   ሀ. አማራ ለ. ኦሮሚያ ሐ. ሲዳማ መ. ደቡብ ኢትዮጵያ

7. የአዲስ አበባ ከተማ አማካይ የከፍታ መጠን ከባህር ጠለል በላይ ስንት ሜትር ነው?

   ሀ. 1500 ሜትር ለ. 2000 ሜትር

   ሐ. 2400 ሜትር መ. 3200 ሜትር

8. በከተማዋ ውስጥ ከፍተኛው ስፍራ የትኛው ነው?

   ሀ. ቦሌ ለ. መርካቶ ሐ. እንጦጦ መ. ፒያሳ

LIVEWORKSHEETS

9. በመሬት ላይ ያለ ርቀት እና በካርታ ላይ ያለ ርቀት ጥምርታ ምን ይባላል?

ሀ. ኬንትሮስ ለ. መስፈርት (Scale)

ሐ. ምልክት መ. አቅጣጫ

10.ስለ ስፍራዎች መገኛ መረጃ የሚሰጥ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የትኛው ነው?

ሀ. ሬዲዮ ለ. ጂ.ፒ.ኤስ (GPS)

ሐ. ቴሌቪዥን መ. መጽሔት

11.አዲስ አበባ በኢትዮጵያ ውስጥ ያላት አንጻራዊ መገኛ የት ነው?

ሀ. ሰሜን ለ. ደቡብ ሐ. ምሥራቅ መ. መሀል

12.ዜሮ ዲግሪ ($0^{\circ}$) ኬክሮስ ምን ተብሎ ይጠራል?

ሀ. ግሪንዊች ለ. የምድር ወገብ (Equator)

ሐ. ሰሜን ዋልታ መ. ደቡብ ዋልታ

## ክፍል ሁለት፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ከሆኑ እውነት ሐሰት ከሆኑ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ

1. ካርታ የአንድን ቦታ ርቀትና ስፋት ለማወቅ ይረዳል፡፡

2. አንጻራዊ መገኛን ለመግለጽ ኬክሮስና ኬንትሮስን እንጠቀማለን፡፡

3. አዲስ አበባ የባህር በር አላት፡፡

4. ትልቁ ሜሪዲያን (Prime Meridian) ዜሮ ዲግሪ ኬንትሮስ ነው፡፡

5. እንጦጦ ከአዲስ አበባ በስተ ደቡብ የሚገኝ ተራራ ነው፡፡

LIVEWORKSHEETS

6. አቅጣጫ ማለት አንድ ነገር ፊቱን ያዞረበት መስመር ማለት ነው፡፡

7. ኬንትሮሶች ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የሚሰመሩ ቀጥ ያሉ መስመሮች ናቸው፡፡

8. የቦሌ አየር መንገድ አካባቢ የአዲስ አበባ ከፍተኛው ቦታ ነው፡፡

9. ጎግል ካርታ (Google Map) መገኛን ለማወቅ የሚረዳ ቴክኖሎጂ ነው፡፡

10. አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዲፕሎማቲክ መዲና ናት፡፡

**ክፍል ሦስት፡ ከዚህ በታች "ሀ" ስር የሚገኙትን በ "ለ" ስር ከሚገኙ መልሶቻቸው ጋር በማዛመድ ትክክለኛዉን ቁጥር በክፍት ቦታው ላይ ፃፉ**

| ረድፍ "ሀ" | ረድፍ "ለ" |
| --- | --- |
| .........መስፈርት (Scale) | 1. የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛ በአሃዝ መግለጫ |
| ..........ኬክሮስ | 2. የካርታ ርቀትና የመሬት ርቀት ንጽጽር |
| ..........አንጻራዊ መገኛ | 3. የአዲስ አበባ ዝቅተኛው ቦታ አካባቢ |
| ..........ፍጹማዊ መገኛ | 4. ከምድር ወገብ በስተሰሜንና ደቡብ የሚለካ |
| ..........ቦሌ | 5. መገኛን ከሌላ ነገር ጋር በማነጻጸር መግለጽ |
| .........እንጦጦ | 6. የአዲስ አበባ ከፍተኛው ቦታ |
| .........መርካቶ | 7. ትልቅ ክፍት የገበያ ቦታ |

LIVEWORKSHEETS